# ስለ ማህበራዊ ቁጥጥር፣ አስገድዶ ጋብቻና በዚህ በኩል የሚደረጉ የእገዛ አገልግሎቶች አጠቃላይ ምልከታ።

ከታች፤ ስለ ማህበራዊ ቁጥጥር፣ እምነትና ማህበራዊ ቁጥጥር፣ አስገድዶ ጋብቻና የቤተሰብ /ወላጆች/ ስምምነት ጋብቻ ተገልጿል። እያንዳንዱ ክፍል በጉዳዩ ላይ የማገናዘብያ ጥያቄን ይዟል። አጠቃላይ የአደጋ ምልክቶችንና ከእምነት ጋር የተያያዙ የአደጋ ምልክቶችንም አካተናል። እርስዎም ሆኑ ሌሎች የሚያውቋቸው ሰዎች እገዛ ከፈለጉ፣ ጥቅል የእገዛ ሃሳቦችን ከስር ያገኛሉ። በዚሁ ርእስ ዙርያም ሌሎች የድረገጽ መረጃዎች በጥቅሉ ይገኛሉ።

## አዎንታዊና አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር።

አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ላይ አንድ ነገር ከማድረግዎ በፊት፣ አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ራሱ ምን ማለት እንደሆነና ምን እንደሚመስል ማወቅ ይጠበቅብዎታል። ማህበራዊ ቁጥጥር በሁሉም ማህበረሰቦችና ባህሎች ያለ ሲሆን በራሱ አሉታዊ አይደለም። የማህበራዊ ቁጥጥር ምሳሌዎች እንደ በቤተሰብ ውስጥ ወላጆች ለልጆቻቸው ጊዜ ሲሰጡ፣ ልጆች በኮምፒተር፣ ቲቪና ሞባይል ስልክ ላይ የሚያሳልፉት ጊዜ መወሰንና ለትምህርታቸው ጊዜ እንዲሰጡ ወይም ሌሎችንም እንዲረዱ ማበረታታት ያሉ ናቸው። አንድ ሰው በሚጠበቅበት መንገድ እንዲያድግ የሚያስተምሩ ያልተጻፉ ህጎችና የህብረተሰብ ልምዶች አሉ፤ ነገር ግን እነዚህ የሚያጠናክሩም የሚገድቡም /የሚያግዱም/ ሊሆኑ ይችላሉ።

ማህበራዊ ቁጥጥር አሉታዊ የሚሆነው፣ አንድ ሰው የህብረተሰቡ ልምድና ባህል እንዲኖረው በሚል ብዙ ጊዜና ለተራዘመ ጊዜ የተለያየ መልክ ያለው ስልታዊ ጫና ሲደረግበትና፣ አፈጻጸሙም በማስፈራራት ወይም እግር በእግር በመከታተል ሲሆን ነው። ቁጥጥሩ አሉታዊ ነው የሚያሰኘው በሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችና፣ በህጻናት /ልጆች/ ኮንቬንሽንና በኖርወይ ህግ እንደተገለጸው ከሰውዬው የግል መብት ጋራ ሲጋጭ ነው።

ወላጆች የልጆቻቸውን ሞባይል ቴሌፎን ነጥቀው፣ እስቲ ሞባይል ከማየት ይልቅ ሌላ ነገር አድርጉ ቢሏቸው አሉታዊ ተጽእኖ አይደለም። ከዚህ ውጪ ግን ወላጆች ከትምህርት ሰአት በኋላ በየቀኑ የልጆቻቸውን ሞባይል እየፈተሹ ልጆቻቸው «ትክክለኛ» ነገር እያደረጉ እንደሆነ ለማረጋገጥ ቢሞክሩ ከባድ የሆነ የአደጋ ምልክት ነው።

## የአዎንታዊና የአሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ልዩነት።

የአዎንታዊና የአሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ልዩነቱ፣ ያው አሉታዊዎቹ አንድ ሰው ራሱን እንዳይሆንና የራሱ ምርጫ እንዳይወስድ የግል ነጻነቱን በስልት ይገድባሉ። ባህርይን /ጸባይን/ ከማበረታታት ይልቅ ይገድባሉ። ለዚህ ምሳሌዎች የሚሆኑ፣ አላግባብ ደጋግሞ የጓደኞች፣ የልብስ፣ የፍቅረኛና የመሳሰሉ ሌሎች የህይወት ምርጫዎችን ለማሰናከል መጣር።

የመንግስት የችግር መፍቻ መርሃ-ግብር «በራስ ህይወት የመወሰን መብት»ን በአሉታዊ የማህበራዊ ህይወት ቁጥጥር የሚገልጸው በዚህ አይነት መንገድ ነው።

«አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር የምንረዳው፣ እያንዳንዱ ሰው ቅቡል የሆነ የቤተሰብ ወይም የቡድን ባህሪይ መያዙን ለማረጋገጥ ሲባል የሚሞከር የተለያየ አይነት ቁጥጥር፣ ጫና፣ ማስፈራራትና ማስገደድ ናቸው። የማህበራዊ ህይወት ቁጥጥሩ መለያው ስልታዊ ሆኖ፣ ከብዙው በጥቂቱ፣ በኖርወይ ህግና በልጆች መብቶች ድንጋጌ የተጠቀሱትን የግለሰብ መብቶችን የሚጻረር መሆኑ ነው።»

አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር እንደ ልምድ የሚተገበረው፣ ሰዎች ያሉበትን ማህበራዊ ቡድን እንዳይተዉ ወይም የቡድኑን የተለመዱ ስርአቶች እንዳይቃወሙ ከመነጨ ፍርሃት ነው። አንድ ሰው የቡድን፣ የቤተሰብ ወይም የጋራ

ልምዶች አለያም የክብር እይታን ከተጻረረ ብዙ ጊዜ እንደ መቀጣጫ ጫናና ማስፈራራት ይደርስበታል። የተለመዱትን ስርአቶችን በመጻረር እንዳይንቀሳቀስ «ለመከላከል» ሲባል የግል ነጻነቱ እንዲወሰን ማድረግም ይኖራል። ልጆች በጣም አለማዊ ወይም «እምብዛ ኖርዌጃውያን» እንዳይሆኑ በመፍራት፣ ወይም ቤተሰቡ ክብርና ዝና የሚያጣበት ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ በሚልም ስጋት የሚደረግም ይኖራል። እንደዛም ሆኖ የሚያስከትለው ውጤት ባብዛኛው አንድ አይነት ነው፤ የራስን መብቶችንና በራስ ህይወት ላይ የመወሰን መብትን ማጣት፣ ወይም በአሳሳቢ ሁኔታዎች- አሰቃቂ የስሜት ምላሾች /traumereaksjoner/፣ የስነ-አይምሮ ጤና እክሎችና አካላዊ ጥቃቶችን ይሆናሉ።

አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር የሚተገበረው ባብዛኛው በቤተሰብ ውስጥ፣ በፍቅር ግኑኝነት፣ በትንንሽ ወይም በትልልቅ ቡድኖችና ህብረቶች፤ እንዲሁም ቤተሰቦቹ ወም ጥንዶቹ እንደ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ በመሰለ የማህበረሰብ ጉድኝት ሲኖራቸው ነው። አንድ ነገር ማስተዋል ጠቃሚ ነው፤ አንድ ቤተሰብ በልጆቹ ላይ አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር የሚያደርገው ቤተሰቡ ራሱ በመንፈሳዊ ጉባኤ፣ በቤተሰባዊ ሃረግ ወይም በማህበረሰብ ጫና ስለሚደርስበት ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ መሰመር ያለበት ጉዳይ አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር «የስደተኞች ችግር» እንዳልሆነ ነው፤ በስደተኞች ቤት ብቻ አይደለም እሚከሰተው፣ ሃይማኖታዊም ይሁኑ አይሁኑ በሁሉም ቤቶች ሊከሰት ይችላል።

**የማስተዋል /ማሰብ/ ጥያቄ፡-**

- አዎንታዊ ማህበራዊ ቁጥጥርን እንዴት እንገልጸዋለን፣ ከአሉታዊ ቁጥጥርስ ድንበሮቹ የት ድረስ ይሄዳሉ?
- አሉታዊ የማህበራዊ ቁጥጥርን በሌላ መንገድ መግለጽ ይቻላል?
- ለምንድ ነው አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ችግር የሆነው?

## እምነት /ሃይማኖት/ ለአሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር እንደ ምክንያት።

አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር የሚገለጽባቸው በተለያዩ መንገዶች ነው፤ ያንን ለመተግበር እንደ ምክንያት የሆኑም እንዲሁ ይለያያሉ፤ ለምሳሌ እምነት ወይም ባህል።

«በኛ እምነት /ሃይማኖት/ እንደዛ ነው» ወይም «በእምነት መጽሃፋችን እንደዛ ነው የተጻፈው» የሚሉ አባባሎች ከህግ ተገዢነት ነጻ አያደርጉም። ምክንያታቸው ሃይማኖታዊ ይሁን ባህላዊ፣ በስልት ነጻነቶችን የመገደብ ልምዶች ወይም ተግባሮች ህገወጥ ናቸው። በእምነት ነጻነት ስም እነኝህን አላስፈላጊ ተግባራት እንዲደረጉ ህግ አይፈቅድም፤ የእምነት ነጻነትም ለነኝህ ተግባራት ጥበቃ አያደርግም፣ የእምነት ነጻነት አማኝ-ግለሰቦችን እንጂ ራሱ ሃይማኖቱን /እምነቱን/ አይደለም የሚከላከለው።

እምነት /ሃይማኖት/ የአዎንታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር ምንጭ ሊሆን ይችላል። የእምነት ማህበረሰቦች፣ ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ማእቀፍ ዙርያ፣ አባሎቹ እርስ በርሳቸው የሚተጋገዙበትና የሚረዳዱበትን ጠንካራ ትስስር ይፈጥራሉ። ብዙውን ጊዜ እምነት /ሃይማኖት/ ማህበራዊ መረዳዳትን የሚያበረታታ የስነምግባር /የሞራል/ ምንጭ ነው፤ ብዙውን ጊዜ፤ ችግር ያለባቸው ሰዎች እገዛ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ ሰዎች ከአልኮል መጠጥንና ትምባሆን እንዲርቁ ወይም በልኩ እንዲወስዱ ይረዳል። እነዚህ በጎ ልምዶች ግለሰቡን ወይም ማህበረሰቡን በሙሉ ሊያሳድጉ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ ሰዎች እነኝህንና ሌሎች ልምዶች እየተከተሉ አፈጻጸሙ ወደ ጫና ይሻገርና ማህበራዊ ቁጥጥሩ አሉታዊ ይሆናል። እንዲህ አይነት ተግባር ሃይማኖታዊ ምክንያት ቢኖረውም ተቀባይነት የለውም። የግል ነጻነት በኖርወይ የህግ ማእቀፍ ውስጥ ጎልቶ የሚታይ መብት ነው፤ ያንድ ግለሰብ የነጻነት ድምበር የሚሄደው የሌላው ነጻነት እስኪሚጀምርበት መስመር ድረስ ነው።

በተወሰነ ዝግ የሆነ የክርስትና እምነት ከባቢ፣ ለምሳሌ፣ ወንዶች የእጀ ጥበብ ስራ እንዲሰሩና ሴቶችም ልጆችን ይዘው እቤት እንዲሆኑ ይጠበቃል። «የተሳሳተ» ትምህርት የመማር ፍላጎቶች ላሳዩ ሰዎች፣ ቤተሰቦቻቸውን እንዳያዩ የሚያካትት የማግለል ማስፈራርያ ይደርስባቸዋል። ሙስሊም ሴቶች ከፍላጎታቸው ውጪ ሂጃብ እንዲያደርጉ ጫና እንደሚደረግባቸው በኖርወይ ብዙ ያነጋገረ ችግር ነው። ጫናው፣ ሴቶች ሂጃብ አድርገው መሄዳቸውንና የቤተሰባቸውን ክብር መጠበቃቸውን ለመቆጣጠር ማስፈራራትና ክትትል በማድረግ ይገለጻል። በጣም ወጣ ሲልም፣ ለምሳሌ አንድ ሰው የቤተሰቡን እምነት /ሃይማኖት/ ለመተው ከሞከረ፣ ወይም በሌላ መንገድ የቤተሰቡን አለያም የቡድኑን ክብር /ዝና/ ካራከሰ፣ ቁጥጥሩ በግድያ ማስፈራራትን ወይም የሃይል ጥቃትን ሊያካትት ይችላል። እዚህ ግልጽ መሆን ያለበት የእምነት ነጻነት ማለት በምንም ነገር አለማመንንና የራስ እምነት መተውንም እንደሚያካትት ነው። እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲከሰት ፖሊስ ወዲያው ሊገባበት ይገባል።

### የማስተዋል /ማሰብ/ ጥያቄ፡-

- እምነትን መሰረት ያደረጉ አሉታዊና አዎንታዊ የማህበራዊ ቁጥጥር ምሳሌዎችን ጥቀስ?
- በእምነታዊ /ሃይማኖታዊ/ ከባቢዎች ባሉና በሌሎች ከባቢዎች ባሉ ማህበራዊ ቁጥጥሮች መካከል ልዩነት አለ ወይ?
- በእምነታዊ /ሃይማኖታዊ/ ከባቢዎች ያሉ አሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥሮች እንዴት ማስወገድ ይቻላል?

# የቤተሰብ (ወላጆች) ስምምነት ጋብቻና አስገድዶ ጋብቻ

የቤተሰብ /የወላጆች/ ስምምነት ጋብቻዎች በብዙ ባህሎችና ሃይማኖቶች አስፈላጊ የነበሩና አሁንም ያሉ ሆነው፤ በተለይ እስከ 1900 ዎቹ ድረስ በጣም የተለመዱ የጋብቻ መንገዶች ነበሩ ። «የቤተሰብ /የወላጆች/ ስምምነት ጋብቻ» እና «የግዳጅ ጋብቻ» የሚባሉ ጽንሰ-ሃሳቦችና በመካከላቸው ያለው ልዩነት ነው ዘመናዊው ጉዳይ።

በ1900 'ዎቹ አመታት የፍቅር ጋብቻ በጣም የተለመደ ሆነ ፤ ይህ፣ ሴቶች ሊመርጡና ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ሊጠብቁ ያበቁዋቸውን ብዙ መብቶች ከመጎናጸፋቸው ጋር ይዛመዳል።

ኖርዌይ ውስጥ የቤተሰብ /የወላጆች/ ስምምነት ጋብቻዎች ሕገ-ወጥነት አይደሉም። እንዲህ አይነት ጋብቻ፤ ቤተሰብ፣ የሚሆንን ወይም የምትሆንን የትዳር ጓደኛ ከመጠቆምና ምክር ከመስጠት ጀምሮ እስከ ራሱ ቤተሰቡ እንደ አሰራር በይፋ የትዳር ጓደኛ የሚመርጥበትና፣ ምርጫውም በተጋቢዎቹ (ሊቀበሉት ወይም ውድቅ ሊያደርጉት) የሚወሰንበት አካሄድ፣ በብዙ ደረጃዎች ይከሰታል። የቤተሰብ /መላጆች/ ስምምነት ጋብቻ እንደ ሂንዱይዝም፣ እስልምና፣ ሲክሂዝም፣ ዩናይትድ-ፋሚሊና ሌሎችም ባሉ ብዙ እምነቶች /ሃይማኖቶች/ ውስጥ ይከሰታል።

አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች ባልፈለጉት ሁኔታ ሰዎች ከተጋቡ ግን አስገድዶ ጋብቻ እንጂ የቤተሰብ /ወላጆች/ ስምምነት ጋብቻ አይደለም። አስገድዶ ጋብቻ ህገወጥ ሲሆን እስከ 6 አመት ድረስ የሚያስቀጣ ነው - በዚህ ውስጥ መሳተፍም እንዲሁ ያስቀጣል። የማስገደድ ጋብቻ ሲባል ማስፈራራት፣ አመጽና የስነ-አይምሮ ተጽእኖን የመሳሰሉትን በመጠቀም የሚደረግ የሃይል ጋብቻ ነው። በአስገድዶ ጋብቻና በቤተሰብ /ወላጆች/ ሃሳብ አቅራቢነት በሚደረግ ጋብቻ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ያስቸግራል፤ ብዙዎች ቤተሰባቸውን ለማስደሰት ብለው፣ ክብርን /ዝናን/ ለመጠበቅ በማሰብና በፍርሃት ከፍላጎታቸው ውጪ ጋብቻውን ሊቀበሉት ይችላሉ። በቤተሰብ /ወላጆች/ የስምምነት ጋብቻ ሁኔታ ሁለቱ ተጋቢዎች ፈልገው እየተጋቡ መሆናቸውንና ጫና እንዳልተደረገባቸው ወይም ማስፈራራትና ማእቀብ አለመደረጉን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

የመንግስት ሰራተኞች የሚጠረጠርን አስገድዶ ጋብቻ ለሚመለከተው የመጠቆም ግዴታ አለባቸው። ይህ በተለይ በትምህርት ቤቶችና በሌሎች የመንግስት ተቋማት ውስጥ የሚሰሩትን ይመለከታል። የሃይማኖት መሪዎች የመንግስት ሰራተኞችን ያክል ለሚመለከተው የመጠቆም ግዴታ የለባቸውም፤ ነገር ግን እንደ ሌሎች የሃገሪቱ ዜጎች ሁሉ፣ የሆነ ህገወጥ ነገር ሲደረግ ለሚመለከተው የማሳወቅ ሞራላዊ ሃላፊነት አለባቸው። ይህ መደረግ ያለበት በአሉታዊ የማህበራዊ ሂወት ቁጥጥር ምክንያት በሚጠረጠር አስገድዶ ጋብቻና የእንክብካቤ እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት ነው። የሴቶች ግርዛት ጥርጣሬ በሚኖርበት ጊዜ፣ በወንጀል ቅጣት ህግ አንቀጽ 284 እንደተጠቀሰው፣ በአማኝ ማህበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ የእምነት መሪዎችና የሃይማኖት አባቶች ራሳቸው በሃይል ለማስቆም ሳይሞክሩ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው። ይህ ማለት «ግርዛቱን መከላከል ካልፈለጉ» በገንዘብ ወይም በእስር እስከ አንድ አመት ድረስ ሊቀጡ ይችላሉ[1]። ለሚመለከተው ማሳወቅና መጠቆም ሲባል ለፖሊስ መልእክት መላክ ወይም ሪፖርት ማድረግ ማለት ነው።

የፍትህ ሚኒስቴር ለሚመለከተው ማሳወቅ ወይም መጠቆም ግዴታ የሚለውን ለአስገድዶ ጋብቻና ለሴቶች ግርዛት ሁለቱንም እንዲያካትት መክሯል። ይህ ማለት ሁሉም ሰው አስገዳጅ ጋብቻ ከመካሄዱ በፊት፣ ከጠረጠረም ሆነ ከሆነ በኋላ፣ ሪፖርት እንዲያደርግ የህግ ግዴታ አለው ማለት ነው። የፍትህ ሚኒስቴሩ የወንጀል ህግን የማሻሻያ ሃሳብ፣ ህጋዊ ያልሆኑ አስገድዶ ጋብቻዎች በአንቀጽ 253 የአስገድዶ ጋብቻ የወንጀል ህግ በኩል እንዲታዩ ጭምር ነው። ባሁኑ ወቅት እንደ ሃይማኖታዊ የሆኑ ያልተመዘገቡ ጋብቻዎች ያሉ፣ በህግ ከተመዘገቡ ጋብቻዎች ውጪ የሚደረጉ ጋብቻዎች፣ ባብዛኛው ከአስገዳጅና ከባድ አስገዳጅ ጋብቻዎች በሚሄዱት በወንጀል ህግ አንቀጽ 251 እና 252 መሰረት ነው ቅጣት የሚበየነው። በፍትህ ሚኒስቴሩ የቀረበው ሃሳብ ላይ ግን እንደ ስነ-አይምሯዊ ጫና የመሳሰሉት ከልክ በላይ በሆኑ ጫናዎች የሚጣልን ቅጣት ጠንካራ እንዲሆን ያደርጋል።

---

[1] ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 284፣ https://lovdata.no/lov/2005-05-20-28/§284

በወቅቱ የህግ ማእቀፍና የህግ ማሻሻያ ሃሳቦች ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት የፍትህ ሚኒስቴር የወንጀል ህግ ማሻሻያ የሚሰማበትን ማየት ያስፈልጋል። የወንጀል ህግ ማሻሻያው ከብዙው በጥቂቱ ህጋዊ የሆኑና ህጋዊ ያልሆኑ አስገዳጅ ጋብቻዎችን፣ የሴቶች ግርዛት፣ ለሚመለከተው የማሳወቅና የመጠቆም እንዲሁም ተያያዥ የሆኑትን ይዳስሰል። የወንጀል ህግ ማሻሻያ ሃሳብ የሚሰማበትን ለማግኘት እዚህ ላይ ይጫኑ።

በ2019 ክረምት «ስለ እምነታዊ /ሃይማኖታዊ/ና መንፈሳዊ ማህበረሰብ አዲስ ህግ» የሚል የህግ ማሻሻያ ሃሳብ መጣ። ህጉና መልእክቱ የመንግስት ድጋፍ ለማግኘት የበለጠ ጥብቅ ቅድመ ሁኔታ እንዲኖር ያደርጋል፤ በዚህም ምክንያት በዮህዋ ምስክሮች የእምነት ማህበረሰብ ውስጥ በህዝባዊ ምርጫ ወቅት ድምጽ የመስጠት መብታቸውን በሚጠቀሙ አባላት ስለሚገለሉና ማእቀብ ስለሚደረግባቸው የመንግስት ድጋፍ እንዳይደረግላቸው የሚል ክርክር ነበረ። የእምነት ተቋማት ሃላፊዎችና የሃይማኖት መሪዎች የሚጠረጠርን አስገዳጅ ጋብቻ ቅቡል በማድረግና ባለማሳወቃቸው ምክንያት፣ ወደፊት ከመንግስት የሚያገኙትን ድጋፍ እንዲያጡ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ማወቁ አስፈላጊ ነው።

## የማስተዋል /ማሰብ/ ጥያቄ፡-

- አስገድዶ ጋብቻ ህገወጥ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
- የአስገድዶ ጋብቻና የቤተሰብ /ወላጆች/ ስምምነት ጋብቻ እንዴት ይለያሉ፣ ድምበሩስ የት ነው?
- ድምበሩ ወደ አስገዳጅነት ሲጠጋ እንዴት አድርገህ መከላከል ትችላለህ?

## ልጆች ወይም ወጣቶች ለአሉታዊ ማህበራዊ ቁጥጥር[2] ሲጋለጡ አንዳንድ አመላካች ነገሮች፡-

- በማህበራዊ ግንኙነት ዝግጅቶች አይሳተፉም
- በማህበራዊ ሚድያዎች ውስጥ የሉም
- ከትምህርት ቤት በቀጥታ ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ
- ከትምህርት ቤት ይቀራሉ
- በታላላቅ እህት ወንድሞቻቸው ወይም በወላጆቻቸው ወደ ትምህርት ቤት ይሸኛሉ፣ ከትምህርት ቤትም ይወሰዳሉ
- በታላላቅ እህት ወንድሞቻቸው፣ በወላጆቻቸው ወይም በዘመዶቻቸው ክትትል ይደረግባቸዋል
- ከትምህርት ሰአት በኋላ የሞባይል ስልካቸው መልእክቶችን አይመልሱም (ይህ ሞባይላቸው መያዙን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል)
- በጂምና በዋና ጊዜ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተሳትፎ አያደርጉም
- በክላስ ጉዞና በላየር-ስኩለ /Leirskole/ አብሯቸው ከሚማሩ ተማሪዎች ጋር ተሳትፎ አያደርጉም
- ለየት ያለ አለባበስ ይጀምራሉ
- ድርብ ህይወት ይኖራሉ። ከትምህርት ሰአት በፊትና በኋላ ልብስ፣ ጌጣጌጥ፣ የራስ መሸፈኛ ይቀይራሉ
- በቤተሰብ ውስጥ ያለ ሌላ ሰው የወጣቶችን ገንዘብ፣ ሞባይልና የሞባይል ኔትባንካቸውን ይቆጣጠራል
- ፍቅረኛ እንዲይዙ ወይም ከጓደኞቻቸው ጋራ እንዲገናኙ አይፈቀድላቸውም፣ ወይም ፍቅረኛም ሆነ ጓደኛ የሚፈቀድላቸው ከቡድናቸው/ሃይማኖታቸው ውስጥ ብቻ ነው።
- ከፍተኛ ትምህርት እንዲጀምሩ ወይም እንዲማሩ አይፈቀድላቸውም
- የፍቅር ግኑኝነት ቢጀምሩ እንኳ ምስጢራዊ አድርገው ይደብቁታል
- ወንድም እህትማማቾቹ ከፍላጎታቸው ውጪ እንዲያገቡ ይደረጋሉ
- እህት ወንድማማቾቹ ጊዚያቸው ሳይደርስ ወደ ውጪ እንዲያገቡ ይደረጋል
- ከትምህርት ቤት በወላጆቻቸው ወይም በጠባቂያዎቻቸው ይወሰዳሉ
- እረፍት ለመውሰድ ሲያመለክቱ ለረጅም ጊዜ ነው
- ትምህርት እስኪጀመር ድረስ ከሄዱበት የእረፍት ቦታ አይመለሱም
- በቤተሰብ ውስጥ ድንገተኛ ለውጥ
- ወደፊት ቶሎ እንዳያገቡ ጊዜ ለመግዛት ብለው ትምህርት ቤት ውስጥ ጥሩ ይማራሉ፣ ይከታተላሉ
- ሌሎችን የሚያስከፋ ባህሪይ፣ ብዙ የሚቆጡና ሁሉ በውስጣቸው የሚይዙ ግልጽ ያልሆኑ
- አስታውስ፡- ለውጥ የሚያሳዩት በተለይ ለጾታ ግኑኝነት እድሜ ሲደርሱ ነው
- ለቀጣይ ጊዜ አያቅዱም ወይም ምንም ትምህርትም ሆነ ሌላ ነገር አይመኙም

---

[2] ከ www.rettentil.no የተወሰደ፣ ግን ትንሽ ከ STL ተጨማሪ የታከለበት

## በእምነት /ሃይማኖት/ ህብረት ውስጥ ያሉ አደገኛ ምልክቶች፦

- አንድ ሰው እምነት የሌለው የመሆን ወይም እምነቱን የመቀየር መብት እንዳለው በግልጽ አይናገሩም።
- የእምነትና የመግለጽ ነጻነቶች እምነቱን /ሃይማኖቱን/ እንጂ ግለሰብን አይከላከሉም ብለው ያምናሉ።
- ውስጣቸው ዝግ ነው፣ ለእምነት አባሎቻቸውና ከነሱ ጋራ የእምነት አባልነት ለሌላቸው የሚናገሩት የተለያየ ነው
- በነሱ ህብረት ውስጥ ለሌለ፣ ወይም ለቆ ለወጣ ሰው ይዘጉታል።
- ስለመብቶች መረጃ አይሰጡም፣ ወይም መብቶችን ይገድባሉ፣ በተለይ ለሴቶች።
- ወቀሳ /ሂስ/ ሲቀርባቸው መቋቋም አይችሉም፣ ሂሱን /ወቀሳውን/ እንደመቀበል ይቆጣሉ
- ለኖርዌይ እሴቶች አሉታዊ አመለካከት አላቸው፣ ለህብረተሰቡ ስለሚሰጡ (እንደ የልጆች ደህንነት ጥበቃ፣ ወላጆች ልጆቻቸውን ባግባቡ እንዲይዙ ስለሚሰጥ የምክር እገዛ እና ሌሎችም) አገልግሎቶች መረጃ አይሰጡም።
- ኖርወይ ህብረተሰብ ለመንፈሳዊነት ክፍት መሆኑን አይናገሩም፤ ነገር ግን ስለ የአለማዊነቱ አደገኝነት ይናገራሉ
- ወደፊት እንደማየት ወደኋላ ወደ ትውልድ አገራቸው ያያሉ።
- ለእምነት ተጽእኖ ሲሉ በትውልድ አገር ረዥም ቆይታን ያበረታታሉ።
- በኖርወይ ህግና በእምነቱ ስርአቶች መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ አይናገሩም።
- ሃይማኖታዊና መንግስታዊ /የዜጎች/ የሚባሉ ሁለት አይነት የጋብቻ ስርአቶች እንዳሉ መረጃ አይሰጡም።
- ለህጋዊ /ኦፊስየላዊ/ የጋብቻ እውቅና አይሰጡም ወይም ጥቅሙ አይታያቸውም።
- አንድ ሰው ብዙ ሚስቶች ለሚያገባበት ስርአት እውቅና ይሰጣሉ፣ ይተገብሩታልም።
- የማትፈልገውን ነገር እንድታደርግ ያስገድዳሉ፣ ይጫናሉ ወይም ያስፈራራሉ።
- ሁሌ ለጋራ የቡድን ጉዳዮች ከግለሰብ ጉዳይ ይልቅ ቅድሚያ ይሰጣሉ፤ ለያንዳንዱ ሰው የግል ነጻነት ቦታ አይሰጡም።
- ሴቶች መገረዝ እንዳለባቸው ሃይማኖታቸው የሚያዝ መሆኑን ይናገራሉ። ግርዛት ስለሚያስከትለው የጤና እክል ያጣጥላሉ።
- ከሌሎች የእምነት ማህበረሰቦችና ከመንግስት ተቋማት ጋራ አይነጋገሩም
- አንድ ጥሩ የእምነት ማህበረሰብ እንዴት መሆን እንዳለበት በግልጽ አይናገሩም።

## እገዛ የምታገኝባቸው የግኑኝነትና የማጣቀሻ ዝርዝሮች፡-

- የልጆች ደህንነት አገልግሎት /ባርነቫርን/ የአስቸኳይ ጊዜ ቴሌፎን፡- 116 111
- ለጥቃት/ወንጀል/ ሲጋለጡ፣ የፖሊስ እርዳታ ማእከል፡- 800 40 008 (www.politiet.no/kontakt-oss/stottesenter-for-kriminalitetsutsatte)
- ቀይ መስቀል ስም አልባ የቴሌፎንና የመልእክት አገልግሎት አለው፡-
  ስልክ በ 815 55 201 ፣ መልእክት በ 926 26 488
- ተረኛ የልጆች ደህንነት አገልግሎት (ባርነቫርንስ-ቫክተን)፡- www.barnevernvakten.no
- «Hjelpekilden» ወይም የልT-ሺልደን የተባለ ድርጅት የወላጆች የግኑኝነት አውታርና የውይይት ቡድኖች አሉት፡- www.hjelpekilden.no
- «Selvhjelp for Innvandrere og Flyktninger (SEIF)» የተባለ ተቋም ለወጣቶች የስልክ ተደራሽነት አለው፡- 97 30 97 00
- Dinutvei.no ያሰባሰባቸው የእገዛ እድሎችና krisesentre በብዙ የአገሪቱ ቦታዎች አሉ፡- www.dinutvei.no/hjelpetilbud
- በተጨማሪም Dinutvei.no እንዴት አድርገህ በማያስታውቅ መልኩ የምትፈልገውን ማሰስ እንደምትችል የሚመራ /የሚረዳ/ በ www.dinutvei.no/nettlesing-uten-spor/4-nettlesing-uten-spor ድረ-ገጽ አለው።

## ሌሎች ልታናግራቸው የምትችል ሰዎች[3] ፡-

- የትምህርት ቤቱ አማካሪ ባለሞያ (Rådgiver på skolen)
- የትምህርት ቤቱ የአናሳዎች አማካሪ ባለሞያ (Minoritetsrådgiver på skolen)
- የትምህርት ቤቱ ነርስ (Helsesøster)
- የልጆች ደህንነት ጥበቃ (Barnevernet)
- Kors på halsen, Røde Kors
- www.ung.no

## ሌሎች አጋዥ አካላትና ተዋናዮች፡-

- RVTS ØST www.rettentil.no
- Integrerings- og mangfoldsdirektoratets (IMDi) side Nora www.imdi.no/nora
- www.stortro.no
- www.fritro.no

[3] www.rodekorstelefonen.no/ekstremkontroll ድረ-ገጽ የተወሰደ